# የእጁ እፍኝ

በ ***ሆሊ ሙዲ***
እ. ኤ. አ. ሜይ 1፥ 2005

# The Hollow of His Hand

ትንቢተ ኢሳይያስ 40፥12 "ውኆችን በእፍኙ የሰፈረ፥ ሰማይንም በስንዝር የለካ፥ የምድርንም አፈር በመስፈርያ ሰብስቦ የያዘ፥ ተራሮችን በሚዛን ኮረብቶችንም በሚዛኖች የመዘነ ማን ነው?"

በአንድ ራእይ ውስጥ፥ አንድ ትልቅ (ግዙፍ) የጎደጎደ እጅ አየሁ። ግራ እጅ ሳይሆን ቀኝ እጅ ነበረ። በመንፈሴ፥ ይህ እጅ **የጌታ እጅ** እንደሆነ ተረዳሁ። ይህ ጎድጎድ ያለ ግዙፍ እጅ መላውን ዓለም ይዞ ነበረ።

"***ወደ እጄ ውስጥ ተመልከቺ፦***" ብሎ ያዘዘኝን አንድ ድምፅ (**የጌታን ድምፅ**) ሰማሁ።

በራእዩ ውስጥ፥ የእጁ ላይኛው ከፍታ ላይ እስከደርስ ድረስ በዝግታና በጥንቃቄ ወደ ግዙፉ እጅ ላይ ስድኽ ራሴን አገኘሁ። ወደዚህ እጅ መዳፍ ውስጥ ወደ ታች ተመለከትሁ። እስኪያስገርመኝ ድረስ፥ የ**ጌታ** እጅ ሕዝብ ይዞ አየሁ።

"***ወደ ታች ሂጂና እነዚህን ሕዝብ ተቀላቀዪ፦***" **ጌታ** ለኔ ተናገረ።

ወደ **ጌታ** መዳፍ ውስጥ ራሴን በጥንቃቄ ማውረድ ጀመርሁ፥ ነገር ግን ተንሸራተርሁ። ከሁሉም ከሌሎቹ ጋር በ**ጌታ** መዳፍ ውስጥ አረፍሁ። እኔም በዙሪያዬ ወዳሉት ሰዎች ዙሪያውን መልከት ማድረግ ጀመርሁ። አንዳንዶቹ ሰዎች በ**ጌታ** እጅ ውስጥ በጣም የተረጋጉ፣ እያረፉ የነበሩ እና በሰላም ነበሩ። ነገር ግን ስለ የት እንደነበሩ የተደናገሩ፣ ደስተኛ ያልሆኑ (የተበሳጩ)ና የፈሩ የመሰሉ ሌሎች ሰዎችን አየሁ።

የት እንደነበሩ ተደናግረው የነበሩት አንዳንዶቹ ሰዎች፥ ከ**ጌታ** የውስጠኛው እጅ ወደ ላይ ለመውጣት እየመከሩ ነበር። ነገር ግን እኔ እንዳደረግሁት እነርሱም መንሸራተት ቀጠሉ፥ እና ተመልሰው ወደ ታች ወደ **ጌታ** መዳፍ ውስጥ ብቻ ይወርዱ ነበር። እነዚህ ሰዎች የበለጠና የበለጠ እየተደናገሩ መጡ፥ እና የበለጠና የበለጠ እየፈሩ መጡ።

ከዛ፥ በ**ጌታ** መዳፍ ውስጥ አንድ ጥላ ወረደ። ከእያንዳንዳቸው ጋር፥ ጥላውን ያስከተለው ምን እንደሆነ ለማየት በፍጥነት ወደ ላይ ተመለከትሁ። **ጌታ** በቀኝ እጁ ላይና ከቀኝ እጁ በላይ ለማስቀመጥ ግራ እጁን እንዳነሣ ማየት አስደንቆኝ ነበረ።

**ጌታ** ግራ እጁን ጎድጎድ አድርጎ ከቀኝ እጁ በላይ ሲያደርገው፥ ተደናግረውና ፈርተው የነበሩት ሰዎች የበለጠ እንኳ እየተደናገሩና እየፈሩ መጡ። እነርሱ መጮኽ ጀመሩ እና በታላቅ ጭንቀት ውስጥ ነበሩ።

በ**ጌታ** መዳፍ ውስጥ የነበሩት የተቀሩት ሰዎች ተረጋግተውና በሰላም መቆየታቸውን ቀጠሉ።

ከዛ፥ የታላቅ ማዕበል (አውሎ ነፋስ) ድምፆች በ**ጌታ** መዳፍ ውስጥ ወደነበርነው ወደ ሁላችንም ጆሮዎች መጣ። የማዕበሉ ድምፅ መነሻው ከምስራቅ ነበር። **ጌታ** ግራ እጁን በቀኝ እጁ ላይ ቢከድንም እንኳ፥ በ**ጌታ** የቀኝ እጅ መዳፍ ታችኛው ላይ የነበርነውን ዝናብ እያራሰን ነበረ።

ማዕበሉ መጦፍ ሲቀጥል፥ በ**ጌታ** የቀኝ እጅ መዳፍ ውስጥ ያለን ሁላችንም በአንድ ላይ ተጠጋጋን። ከማዕበሉ የተነሣ ሁላችንም የራስን ቢሆንም እንኳ፥ በ**እግዚአብሔር** ሌላኛው እጅ ከማዕበሉ ሙሉ ሃይልና ንዴት እየተጠበቅን እንደሆነ እናውቅ ነበረ።

በመጨረሻ፥ የማዕበሉ ድምፅ ቀነሰ። አንዳንዶቹ ሰዎች አንዴ በድጋሜ ከ**ጌታ** የውስጠኛው እጅ ወደ ላይ ለመውጣት ሙከራ ሲጀምሩ፥ **ጌታ** በመደነቅ እንዲህ ሲናገር ሰማሁ፥ “*ራሳችሁን አዘጋጁ፤ ገና አላለቀም! በእጄ ውስጥ ቆዩ እና እናንተ ትድናላችሁ። አትፍሩ፥ ለሚታመኑብኝ ሁሉ እኔ መጠለያ ነኝና።*

*ንዴቴንና ቁጣዬን በምድር አንድ ቦታ ላይ እንዳፈሰስሁ፥ ሕጎቼንና ፍርዶቼን ጥለው በሄዱ የምድር ሌሎች ቦታዎች ላይ እንዲሁ ፍርዴን አፈስሳለሁ። እኔ ፍጹም (just)ና ጻድቅ አምላክ ነኝና፤ ያለ አድልኦ። ፍርዴ በአንድ ሕዝብ (አገር) ውስጥ እንደመታ፥ እንዲሁ የእኔን መንገድና ምክሬን ለመከተል የናቁ (have forsaken) ሌሎች ኃጢአተኛ ሕዝቦችንም (nations) ይመታል።*”

ከዛ፥ ሌላ ማዕበል መታ። የማያልቅ በሚመስል ሂደት (ክንውን) ከሌላኛው ምት በኋላ አንድ ማዕበል ይሆናል። በእነዚህ ማዕበሎች ጊዜ፥ ሌሎች ሰዎች ወደ **ጌታ** እጅ መዳፍ ውስጥ መውረድ ቀጠሉ። እነርሱ ከእያንዳንዱ አገር (nationality)ና ዘር (race) ነበሩ። እነርሱ በ**ጌታ** እጅ ታች ላይ ያለነውን ተቀላቀሉን፥ እና ፈለጉና ከእኛ ጋር መጠለያ አገኙ።

በጣም ረጅም ጊዜ በኋላ የሚመስለው፥ የማዕበሎቹ ድምፆች ቆሙ (ተቋረጡ)። በድንገት፥ ወደ ጥላማው ምስጢራዊ ቦታ (recesses) የ**ጌታ** መዳፍ ውስጥ ደማቅ ብርሃን አበራ። በ**ጌታ** መዳፍ ታችኛው ቦታ ውስጥ ያለነው ወደ ላይ ተመለከትን። ጎድጎድ ባለው በእርሱ ቀኝ እጅ ውስጥ ተጠልለን ያለነውን በማስጠለል ከልሎ ያለውን የእርሱን ግራ እጅ **ጌታ** እንዳነሣ አየን።

ከዛ፥ ተዘርግቶ እንዲቆይ **ጌታ** ቀኝ እጁን በዝግታና በጥንቃቄ ዘረጋ። በ**ጌታ** መዳፍ ውስጥ ታጉረን የነበርነው፥ አሁን ቀጥ ብለን ለመቆም ቻልን። ምድር ላይ አተኩረን ስንመለከት፥ ዓይናችንን በተገናኘው (ዓይናችን በተመለከተው) ጥፋት (ውድመት) ተገርመን እና በጣም ተጨንቀን (stricken) ነበር።

የምድር ቦታዎች በሙሉ ጠፍተዋል።

"*የእኔ ፍርድ በአንድ የተለየ ቦታ ላይ ከመሆኑ ኢያንዳንዱ ጊዜ በፊት፥*" **ጌታ** እንዲህ ሲናገር ሰማሁ፥ "*ያንን ፍርድ እንዲያውጁ የእኔን ነቢያቶች አስነሣለሁ። እኔ ማስጠንቀቂያዎችን ለጻድቅም ለኃጢአተኛም እሰጣለሁ። ሰዎቹ ቢሰሙም ባይሰሙም፤ ፍርዶቹ ያለማስጠንቀቂያ እንዲወርዱ አልፈቅድም። ከእንግዲህ ወዲህ በኃጢአተኛና ጻድቅ ባልሆኑ ሕዝቦች (አገሮች) ላይ የዓይን ቅጽበት አላደርግም* ***(I will no longer wink at sinful and unrighteous nations.)*** *የተናገርሁት በሆነ ጊዜ ሁሉም ያስታውሱና ያምኑ ዘንድ እኔ አስቀድሜ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ።*"

መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙር 46
ተፈጸመ።

በእርሱ፥
Hollie L. Moody

ሆሊ ኤል. ሙዲ

**የእሥራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ፥ የእግዚአብሔር አብ ቃልና ልጅ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ቅዱስ እግዚአብሔር የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ** የባሪያውን የቶማስ ቶሙከዳህታን አካል ተጠቅሞ ተረጎመው።
hithomasgetachew@gmai1.com